# የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር-------/2014

## ስለ መንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የማሕበራዊ መድን ሥርዓትን በማስፋፋት ደረጃ በደረጃ ለዜጎች እንዲዳረስ ማድረግ ከአገሪቷ ማሕበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ አንዱ አካል በመሆኑ፣

የሥርዓቱ ተጠናክሮ መቀጠል ለማህበራዊ ፍትሕ፣ ለኢንዱስትሪ ሰላም፣ ለድህነት ቅነሳ፣ ለምርታማነትና ለልማት ጉልህ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው፣

በሥራ ላይ ያለውን የመንግሥት አገልግሎት የጡረታ ዐቅድ አቅም በፈቀደ መጠን ማጠናከር፣ አዋጆቹን በማሻሻል ማጠቃለልና ለሥራው አፈጻጸም ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድን ቀጣይነትና አስተማማኝነት ማረጋገጥ፣ ፈንዱን በኢንቨስትመንት ማዳበርና ግልጽ የሆነ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ....../2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

NewBusinessEthiopia.com

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት በመንግሥት መስሪያ ቤት፣ በመንግስት የልማት ድርጅት ወይም በመንግሥት በሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በቋሚነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ በመቀጠር በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለው የሚሠራ ሰው ሲሆን የመንግስት ተሿሚዎችን፣የምክር ቤት አባላትን፣የመከላከያ ሠራዊትን እና የፖሊስ አባላትን ይጨምራል፤

2/ "የመንግሥት አገልግሎት"ማለት በመንግሥት ሠራተኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) በተመለከቱ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተፈጸመ አገልግሎት ነው፤

3/ "ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ" ማለት ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታ፣ምክትል ሚኒስትር ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያለው የመንግስት ኃላፊ ነው፤

4/ "የምክር ቤት አባል" ማለት አፈጉባኤ፣ ምክትል አፈጉባኤ እና ማንኛውንም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልን ያጠቃልላል፤

5/ "አፈጉባዔ" ወይም "ምክትል አፈጉባዔ" ማለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔ ወይም ምክትል አፈጉባዔ ነው፤

6/"የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር መሥሪያ ቤት፣ ተቋም ወይም አካል ሲሆን በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መንግስታዊ ተቋማትና የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፤

7/"መንግሥት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታትን ያጠቃልላል፤

8/"ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 ንኡስ አንቀፅ 1 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን በንኡስ አንቀፅ 2 የተቋቋሙትን ሌሎች ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

9/"የመከላከያ ሠራዊት አባል" ማለት በአገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በመከላከያ ሠራዊት መተዳደሪያ ሕጎች መሠረት ተቀጥሮ ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ማናኛውም ሰው ነው፤

10/"የፖሊስ አባል" ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት በፖሊስ መተዳደሪያ ሕጎች መሠረት ተቀጥሮ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ሲሆን የወህኒ (የማረሚያ ቤት) ፖሊስን ይጨምራል፤

11/ "ሲቪል መንግሥታዊ አገልግሎት" ማለት ከመከላከያ ሠራዊት እና ከፖሊስ አባልነት ውጪ በሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

12/ "ወታደራዊ አገልግሎት" ማለት በአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

13/ "የፖሊስ አገልግሎት" ማለት በፖሊስ አባላት የሚፈጸም አገልግሎት ሲሆን የማረሚያ ቤት ፖሊስ አገልግሎትንም ይጨምራል፤

14/"የልማት ድርጅት" ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና ከ50 በመቶ ያላነሰ የካፒታል ድርሻ የመንግሥት የሆነባቸውን ድርጅቶችን ያጠቃልላል፤

15/ "አበል" ማለት የአገልግሎት ጡረታ አበል፣ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል፣ የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የተተኪዎች ጡረታ አበል ሲሆን የዳረጎት አበልን ይጨምራል፤

*16/‹ደመወዝ› ማለት ለሥራ ግብርና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ተቀናሽ የሚሆነው ሂሳብ ሳይነሳለት አንድ ሠራተኛ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ሙሉ የወር ደመወዝ ነው፤*

*17/ “ባለመብት” ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አበል የሚያገኝ ወይም አበል ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሠራተኛ ወይም ተተኪ ነው፤*

*18/ “ተተኪ” ማለት በዚህ አዋጅ አን ቀጽ 40(3) የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል፤*

*19/ “የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዕቅድ” ማለት በዚህ አዋጅ ለሚሸፈኑ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አበል ክፍያ ለመስጠት የተቋቋመ ስርዓት ነው*

*20/‹የጡረታ ፈንዶች› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮና ለሚፈጸም የአበል ክፍያ ተግባር የተቋቋሙ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ፈንዶች ናቸው፤*

*21/‹ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ” ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በመንግሥት በሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ውስጥ በጊዜያዊነት ወይም ለቁርጥ ሥራ ከ60 ቀናት ላላነሰ ጊዜ በመቀጠር በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለበት የሚከናወን ሥራ ሲሆን በቀን ሥራ፣ በጥጥ ለቀማ፣በሸንኮራ አገዳ ቆረጣ እና ሌሎች መሰል በየዓመቱ እየተደጋገሙ የሚከናወኑ ሥራዎችን አይጨምርም፣*

NewBusinessEthiopia.com

*22/ "አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል" ማለት በሕግ ብሔራዊ መለያ ቁጥር ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡*

*23/ “አስተዳር” ማለት የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድን ለማስተዳደር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር ነው፤*

*24/ ”ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማለት” የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ነው፤*

*25/ ‹‹ሰው››ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤*

*26/ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡*

***3/ የተፈጻሚነት ወሰን***

1/ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን የጡረታ ጥቅም የሚመለከተው የአዋጅ ቁጥር 270/1994 ድንጋጌ እና አገሪቷ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፡፡ ይህ አዋጅ በዜግነት ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የመንግሥት ሠራተኞች ተፈጻሚ ይሆናል፣

2/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 52(6) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር653/2001 አንቀጽ 54መሠረት መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን እንዲያጡ የተደረጉ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችንና የምክር ቤት አባላትን በሚመለከት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 19(5)፣ አንቀጽ 20 (2) አንቀጽ21(2)፣ አንቀጽ 22(3) እና አንቀፅ 23(2) ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለማሕበራዊ ዋስትና ምዝገባና መለያ ቁጥር

### 4. ምዝገባ

1/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት መሥሪያ ቤቱ የተቋቋመበትን ሕግ፣ የመንግሥት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር የሞላውን የህይወት ታሪክ፣ ፎርም የተሰጠውን የቅጥር ደብዳቤ እና ሌሎች በአስተዳደሩ የሚወሰኑ መረጃዎችን ለምዝገባ ለአስተዳደሩ ማቅረብ አለበት፡፡

BEHAK
NewBusinessEthiopia.com

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርቡ የምዝገባ መረጃዎች፡-

ሀ) ነባር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችንና የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ሲሆን በአስተዳደሩ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ፣

ለ) ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በኋላ የተቋቋመ የመንግሥት መሥሪያ ቤትን ወይም የተቀጠረ የመንግሥት ሠራተኛን የሚመለከት ሲሆን መሥሪያ ቤቱ በተቋቋመ ወይም ሠራተኛው በተቀጠረ በ60ቀናት ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡

### 5. የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር

1/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ የማሕበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም የመንግስት ሠራተኛው በሌላ አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል የሚሰጥ ብሔራዊ መለያ ቁጥር ካለው ይኸው ቁጥር የማሕበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ጭምር ሆኖ እንዲያገለግል ሊደረግ ይችላል፡፡

2/ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ወደሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሲዛወር ወይም በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት ሲቀጠር የማሕበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥሩን ለተዛወረበት ወይም ለተቀጠረበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የግል ድርጅት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

### 6.የምዝገባ መረጃ ለውጥን ስለማሳወቅ

1/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የራሱንና የመንግሥት ሠራተኛውን የምዝገባ መረጃ የሚመለከት ለውጥ ሲያጋጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ የተከሰተውን ለውጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር አያይዞ ለአስተዳደሩ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ እያንዳንዱ የመንግሥት ሠራተኛ የቤተሰብ ሁኔታን የሚመለከት የመረጃ ለውጥ ሲያጋጥመው ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለሚሠራበት የመንግሥት መስሪያ ቤት በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ባለመብት በምዝገባ መረጃው ላይ ለውጥ ሲያጋጥመው ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለአስተዳደሩ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ ማንኛውንም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የጡረታ ባለመብትን የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለውጥ ማሳወቂያ ሲቀርብ የማሕበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር መጠቀስ አለበት፡፡

5/ የማሕበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በመፍረሱ በመከፋፈሉ ወይም በመቀላቀሉ ምክንያት ሠራተኞቹን እንዲረከብ የተደረገው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በ60 ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለአስተዳደሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

6/ የማሕበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታ ሲዛወር ዝውውሩን ያስፈጸመው መንግስታዊ አካል በ60 ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለአስተዳደሩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

7/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4(1) እና አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 ቁጥር (1) እስከ (3)የተደነገጉት ቢኖሩም በቅድሚያ የተመዘገበውን ዕድሜ ወይም የልደት ዘመን ለመቀየር ወይም ለማሻሻል የሚቀርብ ማንኛውም ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

### 7/ የምዝገባ መረጃን አለማቅረብ የሚያስከትለው ውጤት

በሃቅ BEHAK NewBusinessEthiopia.com

1/ በዚህ ክፍል በተመለከተው መሠረት የምዝገባ መረጃዎችን አደራጅቶ የማይዝና በወቅቱ ለአስተዳደሩ የማያስተላልፍ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚመለከተው ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61 መሠረት ይቀጣል፡፡

2/ በዚህ ክፍል በተመለከተው መሰረት የመረጃ ለውጥን በወቅቱ ለማያቀርብ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለመብት ለተተኪዎቹ የሚወሰነው አበል አስቀድሞ በአስተዳደሩ ተደራጅቶ በተያዘው መረጃ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለጡረታ ዐቅድ፣ፈንዶችና መዋጮዎች

### 8. ስለመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ መቋቋም

የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

### 9. ስለጡረታ ፈንዶች መቋቋም

የሚከተሉት የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል።

1/የሲቪል መንግሥታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ፣

2/ የወታደራዊ እና የፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ፡፡

በሃቅ BEHAK NewBusinessEthiopia.com

### 10. የሲቪል መንግሥታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ መዋጮ

ለሲቪል መንግሥታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ በመንግሥት ሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚደረገው መዋጮ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አስራ አንድ በመቶ፣

2/ በመንግሥት ሠራተኛው ሰባት በመቶ፡፡

### 11. የወታደራዊ እና የፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ መዋጮ

ለወታደራዊ እና ለፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ በመንግሥት ሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚደረገው መዋጮ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሠላሳ ሶስት በመቶ፣

2/ በመንግሥት ሠራተኛው ሰባት በመቶ፡፡

12. የጡረታ መዋጮ ክፍያ

1/ እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደመወዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ የመክፈል ግዴታ አለበት፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተገለጸው የጡረታ መዋጮ ለሠራተኞች የወር ደመወዝ ከተከፈለበት ወር መጨረሻ ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ መደረግ አለበት፤

3/ ከሠራተኞቹ ደመወዝ ሊቀነስ የሚገባውን መዋጮ ሳይቀንስ የቀረ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ክፍያውን ራሱ ለመፈጸም ኃላፊ ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የፌደራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ መዋጮ እንደአግባቡ በገንዘብ ሚኒስቴርና በክልሎች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት/ ፋይናንስ/ ቢሮ ተሰብስቦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ማድረግ አለባቸው፤

5/ በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ /ባለበጀት ያልሆኑ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት ሠራተኞች ወርሃዊ የጡረታ መዋጮ በአስተዳደሩ ወይንም አስተዳደሩ በሚወክላቸው አካላት አማካኝነት ተሰብስቦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል፤

BEHAK
NewBusinessEthiopia.com

6/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀጽ የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ በትክክልና በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ስለመደረጉ በገንዘብ ሚኒስቴር፣የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት /ፋይናንስ/ ቢሮዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ በውክልና የጡረታ መዋጮ በሚሰበስቡ አካላት እና አሰሪ መሥሪያ ቤቶች በመገኘት የመቆጣጠርና ምርመራ (ኦዲት) በማድረግ የማጣራት እንዲሁም በተገቢው ጊዜ ገቢ በማያደርጉት ላይ ሕጋዊ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን ይኖረዋል፤

7/ የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚፈለግባቸውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ገቢ አለማድረጋቸውንና የገንዘቡ መጠን በአስተዳደሩ ሲገለጽለት የገንዘብ ሚኒስቴር የፌዴራሉ መንግሥት ድጎማ ከሚያደርግላቸው በጀት ላይ የመዋጮ ገንዘቡን ቀንሶ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ያደርጋል፤

8/ አስተዳደሩ ወይም ውክልና የተሰጠው አካል ተገቢውን የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሳያደርግ ከ3 ወር በላይ የቆየ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መንግሥት ከሚመድብለት በጀት ወይም በባንክ ካለው ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ እንዲሆን የማስደረግ ሥልጣን ይኖረዋል፤

9/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 ተግባራዊ ለማድረግ ማንኛውም ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም በአስተዳደሩ ወይም በአስተዳደሩ ውክልና በተሰጠው አካል ሲጠየቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀፅ (1) መሠረት የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ለአስተዳደሩ ወይም በአስተዳደሩ ውክልና ለተሰጠው አካል ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9)መሠረት ማንኛውም ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሂሳብ ላይ ቀንሶ በአስተዳደሩ ወይም ውክልና በተሰጠው አካል ገቢ እንዲያደርግ ትዕዛዝ በጽሁፍ ከደረሰው በኋላ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሂሳብ ላይ ገንዘብ ወጪ አድርጎ ቢገኝ ባንኩ ወይም የፋይናንስ ተቋሙ ወጪ እንዲደረግ በፈቀደው የገንዘብ መጠን ልክ ተጠያቂ እና ኃላፊ ይሆናል፤

11/ በጡረታ ዐቅዱ ለተሸፈኑ ሠራተኞች ደመወዝ የሚከፍል የመንግሥት መሥሪያ ቤት የባንክ ሂሳቡ የሚገኝበትን የባንክ ቅርንጫፍ ፣ የፋይናንስ ተቋምና የሂሳብ ቁጥሩን ለአስተዳደሩ በጽሁፍ የማሳወቅ የባንኩ ፣ የፋይናንስ ተቋሙ አድራሻና የሂሳብ ቁጥሩ ሲለወጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ ለአስተዳደሩ በጽሁፍ የመግለጽ ግዴታ አለበት፤

12/ አስተዳደሩ ወይም ውክልና የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) መሰረት ሊሰበሰብ ያልተቻለውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ /አስተዳደሩየ ሚያወጣውን መመሪያ በመከተል/ በቀጥታ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ንብረት በጨረታ በመሸጥ ገቢ የማስደረግ ሥልጣን ይኖረዋል፤

13/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት የሚወሰነው የጡረታ አበል በጡረታ ፈንድ ላይ ለሚያስከትለው ተጽዕኖ የመንግሥት ሠራተኛው በሕጉ መሠረት ጡረታ ለመውጣት ለሚቀረው ጊዜ የመጨረሻ ደመወዙን መሰረት በማድረግ በየወሩ ሊከፈል የሚገባው የጡረታ መዋጮ ታስቦ በቅድሚያ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ገቢ መደረግ አለበት፤

14/ ከኃላፊነት ለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የምክር ቤት አባላት የሚከፈለው የጡረታ አበል በጡረታ ፈንድ ላይ ለሚያስከትለው ተጽዕኖ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ለመድረስ ለሚቀረው ጊዜ በየወሩ ሊከፈል የሚገባው የጡረታ መዋጮ ታስቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ለጡረታ ፈንዱ በቅድሚያ ገቢ መደረግ አለበት፤

NewBusinessEthiopia.com

15/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ በ30 ቀን ውስጥ ገቢ ያላደረገ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በራሱ ገቢ የሚተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት ገቢ ባልተደረገው የጡረታ መዋጮ ላይ ደመወዝ ከተከፈለበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ በባንክ ማስቀመጫ ወለድ መጠን መሠረት ከሚታሰብ ወለድ እና አምስት በመቶ ቅጣት ጨምሮ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፤

16/ ከጡረታ መዋጮ ገንዘብ ላይ ቀንሶ ለአገልግሎት ክፍያ፣ ለገንዘብ ማስተላለፊያ፣ ለዕዳ መክፈያ ወይም ለማንኛውም አገልግሎት መጠቀም የተከለከለ ነው፤

17/ አስተዳደሩ የጡረታ መዋጮ ገቢን ከመሰብሰብና ከማስፈጸም ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ሥራዎች ለሌሎች አካላት ውክልና በመስጠት ማሠራት ይችላል፤

18/ የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከማንኛውም ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

### 13. የጡረታ ፈንዶች አስተዳደር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9የተቋቋሙትን የጡረታ ፈንዶች የሚያስተዳድረው የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር ይሆናል፡፡

BEHAK
NewBusinessEthiopia.com

### 14. የጡረታ ፈንዶች አጠቃቀም

1/ የጡረታ ፈንዶቹ ጥቅም ላይ የሚውሉት፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የጡረታ አበል ክፍያዎች ለመፈጸም፤

ለ) በአስተዳደሩ በሚወሰኑ አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች፤ እና

ሐ) ለአስተዳደሩ አስተዳደራዊ ወጪዎች ብቻ ይሆናል፡፡

2/ የጡረታ ፈንዶች በማናቸውም የዕዳ ክፍያ ምክንያት ሊከበሩ ወይም ሊያዙ አይችሉም፡፡

### 15. የአክቹዋሪ ግምገማ

የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በየአምስት ዓመቱ በሂሳብ ስሌት ባለሙያዎች /አክቹዋሪስት/ እንዲገመገም ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ አገልግሎት ዘመንና የጡረታ መውጫ ዕድሜ

### 16/ የአገልግሎት ዘመን መቆጠር ስለሚጀመርበት ጊዜ

1/ የመንግስት ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመንግሥት ሠራተኛነት ከተቀጠረበት ወይም ከተመደበበት ቀን አንስቶ ነው፤

2/ ወደ መንግሥት ይዞታ በተዛወረ ድርጅት ውስጥ የሚሠራ የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሰረት የሚከፈለውን የጡረታ መዋጮ ሊሸፍን የሚችል ፕሮቪደንት ፈንድ ያለው ከሆነ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሆኖ መዋጮ መክፈል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያለው አገልግሎት ይያዝለታል፣ ሆኖም የፕሮቪደንት ፈንድ የሌለው ከሆነ ድርጅቱ ወደ መንግሥት ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ አገልግሎቱ ይያዝለታል፤

3/ የመንግሥት ሠራተኛው በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በሚሸፈን የግል ድርጅት የፈጸመው አገልግሎት በዐቅዱ መዋጮ መክፈል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይያዝለታል፡፡ ለዚህ አገልግሎት አያያዝ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ የሚያስተዳድረው አካል የሠራተኛውን የግል መረጃና ማስረጃ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለአስተዳደሩ ማዛወር አለበት።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ለተፈጸመ አገልግሎት አያያዝ ከመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ወደ ግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ እንዲሁም በግል ድርጅት ለተፈፀመ አገልግሎት ከግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ወደ መንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ የሚደረገውን የጡረታ መዋጮ ገንዘብ ትልልፍ በተመለከተ ብሄራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

NewBusinessEthiopia.com

### 17. የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠር

1/ የአገልግሎት ዘመን የሚቆጠረው በሙሉ ዓመታት፣ በወራትና በቀናት ታስቦ ነው፤

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ሽፋን ባለው ድርጅት የፈፀመው የአገልግሎት ዘመን በሙሉ ተዳምሮ ይታሰባል፤

3/ ለማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የሚከተለው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፡-

ሀ) ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ አገልግሎቱ በሕግ መሰረት ተራዝሞለት በሥራ ላይ እንዲቆይ የተደረገበት ጊዜ፣

ለ) የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ አበል ከተወሰነለት በኋላ በመንግሥት ውሳኔ ወደ ሥራ ተመልሶ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ሐ) የደመወዝ ክፍያ ሳይቋረጥ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱ ተቋርጦ የቆየበት ጊዜ፣

መ) በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለው ሙሉ ጊዜውን በማናቸውም የመንግሥት አካል ወይም በሠራተኛ ማህበር በተመራጭነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ሠ) በመንግሥት መሥሪያ ቤት በጊዜያዊነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፣

ረ) በመንግሥት ትዕዛዝ መንግሥት ከ50 በመቶ በታች የካፒታል ድርሻ ባያዘበት ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፣

ሰ) በመንግሥት ውሳኔ በዓለም አቀፍ ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፣

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4//ሀ/ የተደነገገው ቢኖርም ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ በምክር ቤት አባልነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፡፡

4/ለማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ መሰረት ለሚያዝለት የአገልግሎት ዘመን የሚከተለው አይታሰብለትም፡-

ሀ) አገልግሎቱ በሕጉ መሠረት ካልተራዘመ በስተቀር የጡረታ መውጫ ዕድሜው ከደረሰበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ የሚሰጠው አገልግሎት፣

ለ) ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችበት ማናቸውም ዓለም አቀፍ ስምምነትና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3//ሠ/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕጋዊ ፈቃድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ የመንግስት ሠራተኛ የኢትዮጵያን ዜግነት ከማግኘቱ በፊት በመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም በጡረታ ዕቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት የሰጠው አገልግሎት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከፊደል ተራ (ሐ) እስከ (ሸ) የተመለከተው ጊዜ በአገልግሎት ዘመንነት ሊታሰብ የሚችለው ሠራተኛው ወይም ተመራጩ መክፈል ያለበትን የጡረታ መዋጮ የአሠሪውን ድርሻ ጨምሮ ራሱ የከፈለ ወይም እንዲከፈልለት ያደረገ እንደሆነ ነው፤

6/ በዚህ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ መሰረት የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፍሎት የተሰናበተ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የግል ድርጅት

BEHAK NewBusinessEthiopia.com

ሠራተኛ እንደገና በመንግሥት ሠራተኛነት የተቀጠረ ወይም የተመደበ ከሆነና የወሰደውን ዳረጎት መልሶ ገቢ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፣

7/ በዚህ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ/ም በፊት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ተደርጎለት የነበረ ሰው እንደገና በመንግሥት ሠራተኛነት የተቀጠረ ወይም የተመደበ ከሆነና የወሰደውን የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ከባንክ የማስቀመጫ ወለድ ጭምር መልሶ ገቢ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፣

8/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሰረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለሕይወት አስጊ በሆኑ የስራ መስኮች የተፈጸመ አገልግሎት እስከ አጠፌታ እንዲቆጠር ሊወስን ይችላል፡፡

### 18/ የጡረታ መውጫ ዕድሜ

1/ የጡረታ መውጫ ዕድሜ የመንግሥት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበውን የልደት ዘመን መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ለመከላከያ ሠራዊት አባላት በሠራዊቱ መተዳደሪያ ሕግ በሚወሰን ዕድሜ፣

ለ) ለፖሊስ አባላት በፖሊስ መተዳደሪያ ሕግ በሚወሰን ዕድሜ፣

ሐ) ለሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች 60 ዓመት፡፡

2/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሠረት በልዩ ሁኔታ ለሚታዩ የሙያ መስኮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው በላይ የሆነ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፣

3/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሠረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለህይወት አስጊ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ ለተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ያነሰ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለአገልግሎት ጡረታ አበልና ዳረጎት

NewBusinessEthiopia.com

### 19. የአገልግሎት ጡረታ አበል

1/ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ከሥራ ሲሰናበት የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

2/ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

3/ ቢያንስ 25 ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጭ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕድሜ ልኩ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፤

4/ ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ መብት መከበሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት አገልግሎቱ ለተቋረጠ የመንግሥት ሠራተኛ ተፈፃሚ አይሆንም፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ሲነሳ ዕድሜው 50 ዓመት የሞላው ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) ወይም /4/ መሠረት አገልግሎቱ የተቋረጠ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሳይደርስ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ይኸው ከተረጋገጠበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡ የሞተ እንደሆነም ከሞተበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ለተተኪዎች አበል ይከፈላል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሀልውና በማክተሙ የሰው ኃይል ብዛቱ ከሚፈልገው በላይ በመሆኑ ወይም ከፕራይቬታይዜሽን ጋር በተያያዘ ከሥራ እንዲሰናበት ከተደረገና አገልግሎቱ ከ25 ዓመት ያላነሰና ዕድሜው ከ50ዓመት ያላነሰ ከሆነ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲወሰን የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልክ ይከፈለዋል፤

### 20. የአገልግሎት ጡረታ አበል መጠን

1/ ለማንኛውም 10 ዓመት ላገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ የሚከፈለው የአገልግሎት ጡረታ አበል መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው የነበረው አማካይ ደመወዝ 30 በመቶ ሆኖ ከ10 ዓመት በላይ ለፈጸመው ለእያንዳንዱ ዓመት አገልግሎት፡-

ሀ) የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ላልሆነ የመንግሥት ሠራተኛ 1.25 በመቶ፣

ለ) ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፖሊስ አባል 1.65 በመቶ ተጨምሮ ይታሰባል፡፡

2/ ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ላገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው የነበረው አማካይ ደመወዝ 15 በመቶ፣ ከአምስት ዓመት በላይ ለተፈጸመ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ዘመን 1.125 በመቶ ተጨምሮ ይታሰባል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የሚወሰነው የአበል መጠን የመንግሥት ሠራተኛው፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊው ወይም የምክር ቤት አባሉ መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው ከነበረው አማካይ ደመወዝ 70 በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደሩ ወቅታዊ የኑሮ ሁኔታን መሰረት አድርጎ ዝቅተኛ ወርሀዊ የጡረታ አበል መጠንና የጡረታ አበል ማስተካከያ ሲያደርግ ከተጠቀሰው መጠን ሊያልፍ ይችላል፡፡

NewBusinessEthiopia.com

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በግል ድርጅቶች ጡረታ አዋጅ በጡረታ ከሚገለልበት ሦስት ዓመት አስቀድሞ ባለው ወር ሲያገኝ ከነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ በ25 ከመቶ የሚበልጥ ዓመታዊ አማካይ ክፍያ ስለሚከፈለው የግል ድርጅት ሠራተኛ የአማካይ የደመወዝ አያያዝ የተደነገገው በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 21. የአገልግሎት ዳረጎት

1/ ከአሥር ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ከሥራ ሲሰናበት የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል፣

2/ ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያነሰ አገልግሎት ያለው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ሲነሣ ዕድሜው 50 ዓመት ወይም በላይ ከሆነ የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል፡፡

## 22/ የአገልግሎት ዳረጎት መጠን

*በዚህ አዋጅ አንቀጽ21 መሰረት የሚከፈለው ዳረጎት፡-*

*1/ የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ላልሆነ የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራ ከተሰናበተበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ1.25 በመቶ የወር ደመወዝ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል፤*

*2/ ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፖሊስ አባል ከሥራ ከተሰናበተበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ1.65 በመቶ የወር ደመወዙ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል፤*

*3/ ለከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ከተነሳበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ1.125 በመቶ የወር ደመወዝ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል፤*

## ***ክፍል ስድስት***

## ***ስለጤና ጉድለት ጡረታ አበልና ዳረጎት***

### ***23. የጤና ጉድለት ጡረታ አበል***

*1/ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል በመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤*

*2/ ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በጤና ጉድለት ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሣ የጤና ጉድለት የጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡*

### ***24. የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መጠን***

*በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሰረት የሚከፈለው የጤና ጉድለት ጡረታ አበል በአንቀጽ 20 መሰረት ይታሰባል፡፡*

### ***25. የጤና ጉድለት ዳረጎት***

*1/ ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ ባለመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ዳረጎት ይከፈለዋል፤*

በሓቅ BEHAK NewBusinessEthiopia.com

2/ ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያነሰ አገልግሎት ያለው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በጤና ጉድለት ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሣ የጤና ጉድለት ዳረጎት ይከፈለዋል፡፡

**26. የጤና ጉድለት ዳረጎት መጠን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሰረት የሚከፈለው ዳረጎት በአንቀጽ 22መሠረት ይታሰባል፡፡

**27.የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ስላለመደረጉ**

የመንግሥት ሠራተኛው አገልግሎት በማናቸውም ምክንያት ቢቋረጥ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይደረግም፡፡

**ክፍል ሰባት**

**ስለጉዳት ጡረታ አበልና ዳረጎት**

**28. ትርጓሜ**

1/"በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፤

BEHAR
NewBusinessEthiopia.com

2/ "በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ"ማለት የመንግሥት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራ ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) የመንግሥት ሠራተኛው ከመደበኛ ሥራው ወይም መደበኛ የሥራ ቦታው ወይም ሰዓት ውጪ ስልጣኑ በሚፈቅድለት የሥራ ኃላፊ የተሰጠውን ትዕዛዝ በመፈጸም ላይ እያለ የደረሰን ጉዳት ፤

ለ) ሥልጣኑ በሚፈቅድለት የሥራ ኃላፊ የተሰጠ ትዕዛዝ ባይኖርም የመንግሥት ሠራተኛው በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ውስጥ የደረሰን ድንገተኛ አደጋ ወይም ጥፋት ለመከላከል በሥራ ሰዓት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጪ በሚፈጽመው ተግባር ምክንያት የደረሰን ጉዳት፣

ሐ) የመንግሥት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለመንግሥት ሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለዚህ ተግባር በተከራየውና በግልጽ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረት ጊዜ የደረሰን ጉዳት፣

መ) የመንግሥት ሠራተኛው ከሥራው ጋር በተያያዘ ግዴታ የተነሳ ከስራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ስራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በሥራው ቦታ ወይም መሥሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ በመገኘት የደረሰበትን ማንኛውንም ጉዳት፣

ሠ) የመንግሥት ሠራተኛው ሥራውን በማከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም በሦስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት፡፡

3. "በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" ማለት የመንግሥት ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታውን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም፤

4/ "መደበኛ ሥራ" ማለት የመንግሥት ሠራተኛው በተሰጠው ኃላፊነት ወይም የሥራ ውል መሰረት የሚያከናውነው ተግባር ነው፤

5/ "መደበኛ የሥራ ቦታ" ማለት የመንግሥት ሠራተኛው የመሥሪያ ቤቱን ሥራ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚያከናውንበት ሥፍራ ነው፡፡

በሃቅ BEHAK NewBusinessEthiopia.com

## 29. በራስ ላይ ጉዳት ስለማድረስ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተመለከተው ተቀባይነት የሚኖረው የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳቱ እንዲደርስበት ሆነ ብሎ ያላደረገው ሲሆን ነው፡፡ በተለይም ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የደረሰ ጉዳት የመንግሥት ሠራተኛው በራሱ ላይ ሆን ብሎ ያደረሰው ጉዳት ሆኖ ይቆጠራል፡-

1/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አስቀድሞ በግልጽ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ፣ ወይም

2/ አካሉ ወይም አዕምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሰክሮ በሥራ ላይ በመገኘት የደረሰ ጉዳት፡፡

## 30. በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታና የአካል ጉዳት መጠን ሠንጠረዥ

1/ አስተዳደሩ አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም፡-

ሀ) የአካል ጉዳት መጠን፣

ለ) እያንዳንዱን በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታን በሚመለከት፡-

(1) የበሽታውን ምልክቶች፣

(2) ለበሽታው መነሻ ይሆናል ተብሎ የሚታመነውን የሥራ ዓይነት ወይም አካባቢ፣

(3) በሽታውን ለሚያሲዘው የሥራ ሁኔታ ለመጋለጥ የሚያስፈልገውን አነስተኛ ጊዜ የያዘ ዝርዝር ሠንጠረዥ በመመሪያ ያወጣል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጣው ሠንጠረዥ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ይሻሻላል፡፡

## 31. ግምት

1/ ከሥራው ቦታ ወይም ከሥራው ዓይነት ጋር የተያያዘ በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በተጠቀሰው የሥራ ቦታ ወይም የሥራ ዓይነት ላይ የተሰማራን የመንግሥት ሠራተኛ የያዘው እንደሆነ በሽታው በሥራ ምክንያት እንደመጣ ይቆጠራል፣

2/ በሥራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ ተይዞ የዳነ የመንግሥት ሠራተኛ በሰንጠረዡ ውስጥ በበሽታው አንጻር በተመለከተው የሥራ ዓይነት ላይ ተመድቦ መስራት በመቀጠሉ በዚያው በሽታ እንደገና ቢያዝ አዲስ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል፣

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ቢኖርም በመደበኛ ሥራው ምክንያት ተላላፊ ወይም ነዋሪ በሽታዎችን በማጥፋት ላይ የተሰማራ የመንግሥት ሠራተኛ በዚሁ በሽታ ከተያዘ በሥራ ምክንያት የመጣ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል፡፡

## 32. ማስረጃ ማቅረብ ስለመቻሉ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 መሠረት በሚወጣው ሠንጠረዥ ውስጥ ያልተመለከተ በሽታ በሥራ ምክንያት የመጣ መሆኑን እንዲሁም በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በአንጻሩ ከተመለከቱት ምልክቶች በተለየ ሁኔታ የተከሰተ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡

## 33. አደጋን ስለማስታወቅ

ከመከላከያ ሠራዊት አባል በስተቀር አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አደጋው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአስተዳደሩ ማስታወቅ አለበት፡፡ ይህ ባለመደረጉ በመንግሥት ሠራተኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት መሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ይሆናል፡፡

BEHAK NewBusinessEthiopia.com

### 34. ስለአካል ጉዳት መጠን አወሳሰን

1/ በሥራ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት መጠን የሚወሰነው ሥልጣን በተሰጠው የሕክምና ቦርድ ነው፣

2/ማንኛውም የሕክምና ቦርድ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት መጠንን የሚተምነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30በሚወጣ ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል።

3/ አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በአንድ የሕክምና ቦርድ የተሰጠ ውሳኔ በሌላ በሕክምና ቦርድ እንደገና እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 35. የጉዳት አበል

በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ10 በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ለደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ እንደሁኔታው የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የጉዳት ዳረጎት ይከፈለዋል፡፡

### 36. የጉዳት ጡረታ አበል

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ10 በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ደርሶበት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል በመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጉዳት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

NewBusinessEthiopia.com

### 37. የጉዳት ጡረታ አበል መጠን

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36መሠረት የሚከፈለው የጉዳት ጡረታ አበል መጠን የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳቱ ከደረሰበት ወር በፊት ያገኝ የነበረው የወር ደመወዝ 47 በመቶ ይሆናል፣፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አበል ሊከፈለው የሚችል የመንግሥት ሠራተኛ በአገልግሎቱ ሊያገኝ የሚችለው አበል በጉዳት ሊያገኝ ከሚችለው የበለጠ ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡

### 38. የጉዳት ዳረጎት

1/ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከ10በመቶ ያላነሰ ከስራ የመጣ ጉዳት ደርሶበት ሥራ ለመስራት የሚችል ከሆነ የጉዳት ዳረጎት ለአንድ ጊዜ ይከፈለዋል፣

2/ የመንግሥት ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ ወይም ኅብረት ስምምነት መሠረት በአሰሪው የጉዳት ካሣ ወይም የመድን ክፍያ የሚከፈለው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰ የጉዳት ዳረጎት አይከፈለውም፡፡

### 39. የጉዳት ዳረጎት መጠን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 መሠረት የሚከፈለው የጉዳት ዳረጎት መጠን የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የወር ደመወዙ በ47 በመቶ በ60 ተባዝቶ የተገኘው ሂሳብ በመንግሥት ሠራተኛው ላይ በደረሰው ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ ነው፡፡

## ክፍል ስምንት

## የተተኪዎች ጡረታ አበልና ዳረጎት

### 40.ጠቅላላ

1/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ፡-

ሀ) የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት ጡረታ አበል በመከፈል ላይ እያለ፣ ወይም

ለ) ቢያንስ 10 ዓመት አገልግሎ በሥራ ላይ እያለ፣ ወይም

BEHAK NewBusinessEthiopia.com

ሐ) በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሕይወቱ ካለፈ ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ይከፈላል፡፡

2/ ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ያለው የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ሕይወቱ ካለፈ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3ሀ/ እና/ለ/ ለተመለከቱት ተተኪዎች ዳረጎት ይከፈላቸዋል፡፡

3/ የሚች ተተኪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) ሚስት ወይም ባል፣

ለ) ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጆች ወይም አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ በሽተኛ ልጅ ሲሆን ዕድሜው ከ21 ዓመት በታች የሆነ፣

ሐ) ልጃቸው ሕይወቱ/ቷ ካማለፉ/ፏ በፊት ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሚች ድጋፍ ይተዳደሩ የነበሩ ወላጆች፡፡

41. የሟች ሚስት ወይም ባል ጡረታ አበል

1/ ለሟች ሚስት ወይም ባል የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል 50በመቶ ይሆናል

2/ የሟች ሚስት ወይም ባል የጡረታ አበል ተወስኖ በመቀበል ላይ እያለች ወይም እያለ ጋብቻ ከፈጸመች ወይም ከፈጸመ፡-

ሀ) ሚስት ዕድሜዋ ከ 45 ዓመት በታች ከሆነ፣ ወይም

ለ) ባል ዕድሜው ከ50 ዓመት በታች ከሆነ ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል ይቋረጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት መቋረጥ የሚገባውን የጡረታ አበል የተቀበለች ወይም የተቀበለ የሟች ሚስት ወይም ባል መልሶ የመክፈል ግዴታ አለባት ወይም አለበት፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ እና /3/ ድንጋጌዎች በአካል ጉዳተኛ ሚስት ወይም ባል ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

5/ ለሟች ሚስት ወይም ባል በዚህ አንቀጽ መሰረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚከፈልበት ሁኔታ ሲያጋጥም አንዱና የሚበልጠው ብቻ ይከፈላል፡፡

በሃቅ BEHAK NewBusinessEthiopia.com

42. የሟች ልጅ ጡረታ አበል

1/ ለሟች ልጅ የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል 20 በመቶ ይሆናል፡፡

2/ ሁለቱም ወላጆቹ ለሞቱበት ልጅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የጡረታ አበል 30 በመቶ ይሆናል፡፡

3/ የጡረታ አበል የሚከፈላቸው ወይም ሊከፈላቸው ይችሉ የነበሩ ሁለቱም ወላጆቹ የሞቱበት ልጅ ከእያንዳንዳቸው አበል 20 በመቶ ይከፈለዋል፡፡ ሆኖም የጡረታ አበሉ ድምር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሊከፈል ከሚችለው ያነሰ አይሆንም፡፡

43. የወላጆች ጡረታ አበል

ለሟች ወላጆች ለእያንዳንዳቸው የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል 15 በመቶ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከወላጆች ሌላ ተተኪ ከሌለ 20 በመቶ ይሆናል፡፡

**44.የተተኪ ዳረጎት**

ለማንኛውም ተተኪ የሚከፈለው ዳረጎት ለሟች በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈለው ይገባ ከነበረው ዳረጎት እንደአግባቡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41(1) ወይም አንቀጽ 42 በተወሰነው በመቶኛ ተባዝቶ ይታሰባል፡፡

**45. የተተኪዎች አበል ገደብ**

1/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 41 እስከ አንቀጽ 44 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ለተተኪዎች የሚከፈለው አበል ድምር ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል ከነበረው አበል መቶ በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡ ከተጠቀሰው መጠን በልጦ ከተገኘ ግን ከእያንዳንዱ ተተኪ አበል ላይ ተመጣጣኝ ቅናሽ ይደረጋል፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተተኪዎች ጡረታ አበል ከተስተካከለ በኋላ የተተኪዎች ብዛት ከቀነሰ የአበሉ መጠን እንደገና ይስተካከላል፡፡

NewBusinessEthiopia.com

## ክፍል ዘጠኝ

## አበልን የሚመለከቱ የወል ድንጋጌዎች

**46. ስለዝቅተኛ የጡረታ አበል መጠንና የአበል መሻሻል**

አስተዳደሩ ወቅታዊ የኑሮ ሁኔታንና የጡረታ ፈንዱን የመክፈል አቅም በማገናዘብ ዝቅተኛ ወርሃዊ የጡረታ አበል መጠንና የጡረታ አበል ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

**47. የጡረታ አበል አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ**

1/ የጡረታ አበል የሚከፈለው በየወሩ ይሆናል፣

2/ የአገልግሎት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የመንግሥት ሠራተኛው በዕድሜ ለጡረታ ብቁ ከሆነበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፣

3/ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መታሰብየሚጀምረው የመንግሥት ሠራተኛው በጤና ጉድለት ምክንያት መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፤

4/ የጉዳት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የመንግሥት ሠራተኛው በጉዳት ምክንያት መስራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፤

5/ የተተኪዎች ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው ባለመብቱ ሕይወቱ ካለፈበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፤

6/በዚህ አዋጅ ከተደነገገው የጡረታ መውጫ ዕድሜ በላይ በመንግሥት ሥራ ላይ ቆይቶ የሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ የጡረታ አበል ክፍያ መነሻ የሚታሰበው የመንግሥት ሠራተኛው ከመንግሥት ሥራ አቋርጦ የጡረታ አበል ክፍያ ጥያቄ ለአስተዳደሩ ካቀረበበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ይሆናል።

በሐቅ BEHAK NewBusinessEthiopia.com

**48. የዳረጎት አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ**

1/ ማንኛውም ዳረጎት የሚከፈለው በአንድ ጊዜ ነው፡፡

2/ የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የመንግሥት ሠራተኛው ከሥራ ከተሰናበተበት ቀጥሎ ባለው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ነው፡፡

3/ የጉዳት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የመንግሥት ሠራተኛው ላይ ጉዳት ስለመድረሱና መጠኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

**49. የይርጋ ጊዜ**

1/ ማንኛውም የውዝፍ አበል ወይም የዳረጎት ክፍያ ጥያቄ በሦስት ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል።

2/ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ መጠቀም ከሚችልበት ቀጥሎ ካለው ቀን አንስቶ ነው፡፡

3/ በሚከተሉት ምክንያቶች የባከነ ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር አይታሰብም፡፡

ሀ) ባለመብትነቱን ለማረጋገጥ የተጀመረ የፍርድ ቤት ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ የወሰደው ጊዜ፣

ለ) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት መረጃ የማስተላለፍ ግዴታውን በወቅቱ ባለመወጣቱ ያለፈው ጊዜ

ሐ) ፈንዱ የቀረበለትን የክፍያ ጥያቄ መርምሮ ለመወሰን የወሰደው ጊዜ፡፡

**50 አበል የማግኘት መብትን ማስተላለፍ ስላለመቻሉ**

አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ሊተላለፍ አይችልም፡፡

**51 ስለአበል በሕግ መከበር**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ አበል፡-

1/ ለመንግሥት ገቢ የሚሆን መቀጮ፣ ግብር ወይም ቀረጥ ለመክፈል፣ ወይም

2/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታን ለመወጣት በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር በሌላ ዕዳ ምክንያት አይከበርም፡፡

3/ የማሕበራዊ ጤና መድህን አዋጅ ቁጥር 690/2002 አንቀጽ 9 እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌ ቢኖሩም ለማሕበራዊ ጤና መድህን የሚሰበሰብ መዋጮ በየወሩ ከጡረታ አበል ላይ ተቀንሶ ለማሕበራዊ ጤና መድህን ፈንድ ገቢ ይደረጋል፡፡ ሆኖም፡-

ሀ) የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በሠራተኛነት በመቀጠር ደመወዝ የሚያገኝ ከሆነ የጤና መድህን መዋጮ የሚቀነሰው በየወሩ ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ ብቻ ነው፡፡

ለ) የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት የተተኪም ጡረታ አበል የሚያገኝ ከሆነ የጤና መድህን መዋጮ የሚቀነሰው በራሱ ከሚያገኘው የጡረታ አበል ብቻ ነው።

**ክፍል አሥር**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

BEHAK NewBusinessEthiopia.com

### 52. የመብቶች ግንኙነት

1/ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ከተቀጠረና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18(1) (ሐ) የተደነገገው ጡረታ መውጫ ዕድሜ ያልደረሰ ከሆነ አዲሱ አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተደምሮ ይታሰብለታል፡፡ ሆኖም የአገልግሎት የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት እንደገና በመቀጠር የፈጸመው አገልግሎት ተደምሮና ተሻሽሎ አበል የሚከፈለው የሠራተኛው ዕድሜ 60 ዓመት ከሚሞላበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደገና የታሰበው አበል ከቀድሞው አበል ያነሰ ከሆነ የቀድሞውን አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ወደ ሥራ በመመለስ ለተፈጸመ አገልግሎት የሚከፈል አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይኖርም፡፡

3/ በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ባለመብት በዚህ አዋጅ መሠረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚያገኝበት ሁኔታ ሲያጋጥም ሊከፈል የሚገባው የአበል መጠን አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

4/በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከግል ወደ መንግሥት ይዞታ በተዛወረ ድርጅት ድርጅቱ ከመዛወሩ በፊት ሲከፈል የነበረ ወርሃዊ የጡረታ አበል በዚህ አዋጅ መሰረት ተስተካክሎ ይከፈላል፡፡

5/ ከ10 ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ላላቸው ወይም ከአምስት ዓመት ያነሰ አገልግሎት ኖሯቸው አገልግሎታቸው ሲቋረጥ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ላይ ለደረሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የምክር ቤት አባላት አበል አወሳሰን የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ያልሆኑ የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 55 መሰረት መብቶችና ጥቅሞቹ እንዲቋረጡ የተወሰነበት ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19(5) ወይም አንቀፅ 23(2) መሰረት የሚከፈለው የጡረታ አበል ይቋረጣል፣

7/ ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ቀን አንስቶ ወደ ፊት ዕድሜው 60 ዓመት ከመሙላቱ በፊት በራስ ፍቃድ የአገልግሎት የጡረታ አበል መቀበል የጀመረ የመንግሥት ሠራተኛ በዚያው የመንግስት መሥሪያ ቤት (ድርጅት) ከተቀጠረ ይከፈል የነበረው የጡረታ አበል ይቋረጣል፡፡

### 53. መረጃ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ

BEHAK NewBusinessEthiopia.com

1/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች መሠረት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ እያንዳንዱን የመንግሥት ሠራተኛ የሚመለከቱ መረጃዎችና ማስረጃዎች ማሰባሰብ፣ ማጠናቀር፣ ማደራጀትና በአስተዳደሩ በሚወሰነው ጊዜና ቅጽ መሰረት ለአስተዳደሩ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

2/ ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማስረጃ እንዲልክ ወይም ቀርቦ አስተያየትና መረጃ እንዲሰጥ በአስተዳደሩ ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3/ የሚመለከታቸው አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(5) በሚሰጥ ውክልና መሠረት የጡረታ መዋጮ በመሰብሰብ ረገድ ከአስተዳደሩ ጋር የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

## 54. የአስተዳደሩውሳኔዎች

1/ በዚህ አዋጅ መሰረት ለሚሰጥ ለማናቸውም ዓይነት አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላታቸው የሚረጋገጠውና የአበሉ ዓይነትና መጠን የሚወሰነው በአስተዳደሩ ይሆናል፡፡

2/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ውሳኔ የሚሰጠው የራሱን የመረጃ ማህደር፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 53 መሠረት የሚተላለፉትን መረጃዎችና እንደ አግባቡ ባለመብቱ የሚያቀርባቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

3/ በአስተዳደሩ የመረጃ ማህደርና በቀረበለት ማስረጃ መካከል ልዩነት ቢፈጠር ተቀባይነት የሚኖረው ማስረጃ በአስተዳደሩ ይወሰናል፡፡

BEHAK NewBusinessEthiopia.com

## 55. ውሳኔን እንደገና ስለመመርመር

1/ ቅሬታ ያለው ባለመብት በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በራሱ አነሳሽነት አስተዳደሩ ቀደም ብሎ የሰጠውን ውሳኔ እንደገና ለመመርመር ይችላል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 የተደነገገው ቢኖርም አስተዳደሩ ውሳኔውን እንደገና ሲመረምር የአበል መሰረዝ፣ መቀነስ ወይም መቋረጥ ሊያስከትል የሚችል በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ሊሰረዝ፣ ሊቀነስ ወይም ሊቋረጥ በሚገባው አበል መጠን ክፍያው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይችላል፡፡

3/የዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 ድንጋጌ ቢኖርም እንደገና በተደረገ ምርመራ የጡረታ አበል እንዲቀነስ አስተዳደሩ ከወሰነ ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌ ውጪ ያለአግባብ የጡረታ አበል ከተከፈለ አስተዳደሩ ከባለመብቱ አበል ላይ እየቀነሰ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## 56. ስለ ይግባኝ

1/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 ወይም አንቀፅ 55 መሰረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ባለመብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 ለተቋቋመው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

2/ የይግባኝ አቤቱታ ለጉባዔው መቅረብ የሚችለው ይግባኝ በሚባልበት ጉዳይ ላይ ውሳኔ በተሰጠ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

3/ ጉባዔው የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈጸም ከወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አንፃር መርምሮ የአስተዳደሩን ውሳኔ መለወጥ፣ ማሻሻል ወይም ማጽናት ይችላል፡፡

4/ ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ሆኖም የጉባዔው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለው ብሎ የሚያምን ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

## 57. የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56መሠረት የሚቀርቡ ይግባኞችን እየመረመረ ውሳኔ የሚሰጥ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ የጉባዔው አደረጃጀትና የአባላት አሰያየም በመንግሥት ይወሰናል፡፡

3/ ከጉባዔው አባላት አብዛኞቹ በጉባዔው ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

4/ የጉባዔው ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው በተገኙ አባላት በአብላጫው ድምጽ ሲደገፍ ነው፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉባዔው የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

NewBusinessEthiopia.com

## 58. ከግብር ነፃ ስለመሆን

በዚህ አዋጅ መሰረት በሚከፈል የጡረታ አበል ፣ በሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮ እና ከጡረታ ፈንድ ኢንቨስትመንት በሚገኝ ትርፍ ላይ ግብር አይከፈልም፡፡

## 59. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

2/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 የተጠቀሰውን የአካል ጉዳት መወሰኛ ሠንጠረዥ እስከሚያወጣ ድረስ የሕክምና ቦርዶች የሚከተሉት አሰራር ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀት (5) እንደተጠበቀ ሆኖ ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም በፊት በመንግስት መሥሪያ ቤት፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት እና በመንግስት በሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ለተወሰነ ጊዜ ያገለገለ ሠራተኛ ከሃምሌ 01 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ይህ አዋጅ በሚጸናበት ቀን በሥራ ላይ ለሚገኝና ተገቢውን የጡረታ መዋጮ ለከፈለ ሠራተኛ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4/የአዋጁ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (4) እና አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም በፊት ቢያንስ 25 ዓመት አገልግሎ በተለያየ ምክንያት ሥራውን ላቋረጠ ሠራተኛ የአዋጁ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ቀደም ሲል የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የጡረታ አበል ተጠቃሚ ባለመብት ሆኖ በወንጀል ጥፋት ምክንያት ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ተፈርዶበት የዘለቄታ የጡረታ መብቱን ያጣ ባለመብት ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም አንስቶ ውዝፍ አበል ሳይጨምር ለወደፊት የጡረታ አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

6/ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ በሥራ ላይ ለሚገኝ ወይም በኋላ ለሚቀጠር የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) በተገለጸ ምክንያት ያልተያዘለት አገልግሎት ለወደፊት ከአዲሱ አገልግሎቱ ጋር ተደምሮ እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

## 60. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

በሃቅ BEHAK NewBusinessEthiopia.com

2/ አስተዳደሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 61. ቅጣት

የያዘውን ማስረጃ በዚህ አዋጅ መሰረት ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የዚህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንብ እና መመሪያዎች ድንጋጌ አፈፃፀም የሚያሰናክል ተግባር የፈጸመ ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግ ተጠያቂ ይሆናል ፡፡

## 62. የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

1/ የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ) የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003(በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ) ፣

ለ) የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር የወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 አንቀጽ 12 እና የጡረታ ሽፋንን የሚመለከተው የአንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ፣

ሐ) ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብትና ጥቅሞች አዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 12 እና አንቀጽ 21፣

BEHAK
NewBusinessEthiopia.com

2/ ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች ወይም የአሰራር ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

## 63. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ _______________ ቀን _______ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ……………………ዓ/ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት